# ቀስተ ደመና ሬድዮ

## ትችት

(27.12.02)

# እውነትም ሰዶ ማሳደድ እንዳይሆን!

ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ በተባለው ስብስብ ውይይት ተብሎ በተዘጋጀው መድረክ የወያኔ መንግስት አንዱ አላማ እንሳተፍ አንሳተፍ በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የተቃዋሚዎች ሰፈር እንዲተራመስና እርስ በርሱ እንዲቦጫጨቅ ለማድረግ እንደነበረ ግልጽ ነው። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ይህ ሴራ የተሳካ ይመስላል። ሌሎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንሳተፍም ሲሉ ኢዴፓና ኢዲዩ ብቻቸውን ተሳትፈዋል። በዚህም የተነሳ ብዙ መወነጃጀሎች ተከስተዋል ። አንሳተፍም ያሉትን እንደ ቁርጠኛ ተቃዋሚ አርጎ የማቅረብና የተሳተፉትን ደግሞ ለጠላት ያደሩ ወይም ለማደር የቁዋመጡ ከሃዲዎች አርጎ የማቅረብ አሳፋሪ አዝማሚያ እየታዘብን ነው።

በበኩላችን ዋናውን ጥያቄ በመሳተፍና ባለመሳተፍ ዙሪያ አድርገን አናየውም። ዋናው ጥያቄ ዛሬ አገራችንንና ህዝባችንን ወጥረው ከያዙት ጥያቄዎች አንጻር ባለመሳተፍ ምን ተገኘ በመሳተፍስ ምን ቁምነገር ተሰራ የሚለው ጥያቄ ነው። ለዚህ ጥያቄ ተገቢ መልስ ሳንሰጥ ያልተሳተፉትን ባለመሳተፋችሁ አበጃችሁ አንላቸውም። ለዚህ ጥያቄ መልስ ሳንሰጥ እነኢዴፓን በዚህ መድረክ በመሳተፋቸው አናወግዛቸውም። የሰላም ትግል እስከተባለ ድረስ ሌላው ቀርቶ ወያኔ በቀን ሃያ አራት ሰአት በሚቆጣጠረው መገናኛ ብዙሃን አስርም ሆነ ሃያ ደቂቃ መልእክት ለማስተላለፍ አጋጣሚ ከተገኘ በዚህ ተጠቅሞ ለህዝብ መልእክት ለማስተላለፍ መሞከር ከሃዲ ለሚሉት ከባድ ውንጀላ አያስዳርግም።

መድረኩም ውይይቱም ፋይዳ ቢስ ነው ከወዲሁ እነአቶ መለስ በአሸናፊነት እንዲወጡ የተመቻቸ ነው ከተባለ ወያኔዎች ሙሉ በሙሉ «በአሸናፊነት» እንዲወጡ በተመቻቸው ባለፈው ምርጫ ለምን ተሳተፍን? ወያኔዎች ደግመው በርግጥ በአሸናፊነት ወጣን በሚሉበት በመጭውስ ምርጫ ለምን እንሳተፋለን? ባለፈው ምርጫ አንዳንድ ወገኖች «በዚህ ግርግር መሳተፍ ለወያኔ መስራት ነው» ሲሉ ተቃውመናቸው ነበር። ውጤቱ ምን እንደሚሆን ሳናጣው የቻለ ሁሉ በምርጫው እንቅስቃሴ ይሳተፍ ብለን ጥሪም አድርገን ነበር። ይህም በመደረጉና በእንቅስቃሴው ሳቢያ ተቃዋሚዎች ህዝባዊ የሆነ መልእክታቸውን ማስተላለፍ በመቻላቸው ወያኔ ምንም እንኩዋን «በአሸናፊነት» ወጣሁ ቢልም በህዝብ ፊት ይበልጥ ተጋልጡዋል። አሁንም ቢሆን ተቃዋሚዎች ህዝባዊ መልእክታቸውን ለማስተላለፍ በዚህ ወያአኤያዊመድረክ በመጠቀማቸው ብቻ ለወያኔ ቅባሎትን ያስገኛል ብሎ መገመት ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን አንዳንዶች ለህዝባችን የማሰብና የማመዛዘን ችሎታ ያላቸውን ንቀትን የሚያንጸባርቅ አካሄድ ነው።

ከዚህ ተነስተን ወደ ዋናው ጥያቄ ስንገባ በዚህ በሰሞኑ የነኢንተር አፍሪካ ግርግር ባለመሳተፍ ምን የተገኘ ነገር አለ ለሚለው ጥያቄ መልሱ ምንም የለም የሚል ነው። በነኢዴፓ መሳተፍስ ምን ተገኘ ለሚለውም ጥያቄ መልሱ ይኸው ነው። ምንም የረባ ነገር አልተገኘም። የረባ ነገር አልተገኘም የምንለው እነኢዴፓ በዚህ መድረክ ተጠቅመው ከወያኔ ፖለቲካ አንጻር ያላቸውን አማራጭ ለህዝብ አላቀረቡም ለማለት አይደለም። አቅርበዋል። አማራጭ ማቅረብ የተቃዋሚ ተግባር ነውና በዚህ በኩል ሃላፊነታቸውን ተወጥተዋል ማለት ይቻላል። ክርክሩ መሆን ያለበት ይህ ያቀረቡት አማራጭ ያዋጣል ወይስ አያዋጣም በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ነው። ለዚህም ጥያቄ ያለን መልስ የቀረበው አማራጭ ዛሬ በሃገራችን ባለው ተጨባጭ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ የሚያዋጣ አይደለም የሚል ነው ። በተቃዋሚዎች መሃከል መደረግ ያለበት ክርክር በዚህ ጥያቄ ዙሪያ መሆን ሲገባው ማንም ከቁም ነገር ጽፎ ያነሳው የለም።

ዛሬ ሃገራችን ፊት ከደርግ ዘመን የከፋ የርሃብ አደጋ ተደቅኑዋል። የዚህ ርሃብ አ
ስከፊነት ለአደጋው የተጋለጡት ዜጎች ቁጥር ካለፊው እጥፍ ድርብ በመሆኑ ብቻ አይደለ
ም። ለህዝባችን መጭውን ጊዜ እጅግ ሊያጨልሙ የሚችሉና ርሃብን ከምድራችን ገጽ ለ
ማጥፋት የምናደርገውን ጥረት ለመጭወቹ ብዙ አስርት አመታት ሊያኮላሹ የሚችሉ ሌሎ
ች ሁለት መዘዞች አሉ።

የመጀመሪያው አደገኛ ክስተት በዚህ እርሃብ በማስታከክ በመቶ ሽ ቶን እየተቆጠረ
ወደ ሃገር የሚገባውን ከተቀየረ ዘር የሚመረተውን የእርዳታ እህል የሚመለከት ነው። በዚ
ህ ጉዳይ ከጥቂት ሳምንታት በፊት «የእርዳታው እህል እውን መርዝ ነው?» በሚል ርእስ
ተችተንበታል። እንዲህ አይነቱ እህል ሲበላ መርዘኛነቱ ባይረጋገጥም ሲዘራ ግን ሊያመጣ
የሚችለውን መዘዝ አመልክተናል። ይህ በታላላቅ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ላቦራቶሪ ውስ
ጥ ተቀምሞና ተቀይሮ የሚሰራ ዘር በአንድ በኩል ሲዘራ አፈሩን የማምከን አደጋ አለው።
ሁለተኛ ደግሞ ተመርቶ ቢበላም እንደገና ቢዘራ አይበቅልም። ይህም ማለት ገበሬው በየአ
መቱ ለማምረት ዘር ከነዚህ ኩባንያዎች ለመግዛት ይገደዳል ማለት ነው። አንዳንድ ተችዎ
ች ይህንን ክስተት ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በአለም ገበሬዎች ላይ የከፈቱት የባዮ ቴክኖ
ሎጂ ጦርነት ብለው እስከመጥራት ደርሰዋል።

ይህንን መዘዝም በመፍራት እንደኛ በርሃብ የተጠቁ የደቡባዊ አፍሪካ አገሮች መጀ
መሪያ ላይ ለምንና እንዴት ይህ እህል በርዳታ ስም ወደ ሃገራቸው እንዳይገባ እንደተቃወ
ሙና በሁዋላ ደግሞ ቢያንስ ከዚህ እህል የተወሰነው ክፍል በገበሬዎች ተመልሶ እንዳይዘ
ራ ለመከላከል ወደ ሃገር የሚገባው በዱቄት መልክ ብቻ እንዲሆን ስምምነት መደረሱን
ጠቁመናል። የኛ ሃገር ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሆኑ የሲቢክ ማህበረሰቡ አባላት በዚህ በአፍ
ሪካ ብቻ ሳይሆን በመላው አለም እየተጡዋጡዋፈ በመጣው ውዝግብ ውስጥ ገብተው የሃ
ገራችንን ገበሬዎች ህልውና ጥያቄ ውስጥ በሚያስገባና የምድራችንን መምከን ሊያስከትል
በሚችል ጉዳይ ላይ ምንም ያሉት ነገር የለም። የነኢዴፓ ተሳትፎ የወያኔ መሪዎች በተለ
ይ እንደ ሃይብሪድ ኢንተርናሽናል አይነት ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ጋር በመመሳጠር በመ
ፈጸም ላይ ስላሉት ደባ ለአንዲት ደቂቃ እንኩዋን ፍንጭ ቢሰጥ ኖሮ ፍሬያማ ተሳትፎ ይ
ሆን ነበር እንላለን። ይህ ግን አልሆነም።

ሁለተኛው ጥያቄ በመሬት ስሪቱ ለውጥ ጉዳይ ከፊታችን የተደቀነውን አደጋ የሚ
መለከት ነው። በተከሰተው የርሃብ አደጋ ሳቢያ ይህ ጥያቄ አግጦና አፍጦ ቀርቡዋል። መ
ሬት የግል ሃብት ይሁን ወይስ ከመሸጥና መለወጥ መብት በመለስ ለገበሬው የይዞታ ዋስት
ና በሚያረጋግጥ ለውጥ እንወሰን? በዚህም ጉዳይ ባለፈው ሳምንት የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊ
ስት ንቅናቄ (መኢሶን) ልሳን የሆነው የሰፊው ህዝብ ድምጽ «መሬትየግል ሃብት? ገጠሩንም
ለወያኔዎች እንዳናስረክብ!» በሚል ርእስ ያቀረበውን ሰፊ ትችት አስደምጠናል። በዚህ ት
ችት ላይ እንደተጠቆመው ዛሬ የገበሬውን የማምረት ቅስም ሰብሮ ሃገራችንን ለተደጋጋሚ
ርሃብ የዳረጋት መሬት የመንግስት በመሆኑ አይደለም። ከዚህ ይልቅ ለርሃቡ ተጠያቂ የሚ
ሆነው ወያኔ በገጠሩ የፖለቲካ ቁጥጥሩን ለማረጋገጥ የይዞታ ዋስትና ነስቶ በየወቅቱ መሬት
ን መልሶ መላልሶ በማደላደል ሂደት የፈጠረው አለመረጋጋት ነው።

ገበሬው የሚያርሳት ማሳ ለልጅና ለልጅ ልጁ ቀርቶ የዛሬ አምስት አመት እንኩዋን
የሱ መሆኑዋን እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ ያለችውን ገንዘብም ሆነ ጉልበት አስተባብሮ መ
ሬቱን ለመንከባከብም ሆነ ለማሻሻል የሚገፋፋው ምንም ነገር የለም። የይዞታ መረጋገጥ በ
ኢኮኖሚውም ሆነ በአካባቢ ጥበቃ መስክ የሚያመጣውን በጎ ውጤት ወያኔዎች ሳይቀሩ ያ
ውቁታል። ችግራቸው ይህ ለውጥ ከተደረገ ገበሬው ከነሱ የፖለቲካ ቁጥጥር ሙሉ በሙ
ሉ ነጻ ይወጣል። ይህ ከሆነ ደግሞ እንዳሁኑ በነጻ ምርጫ ስም እያወናበዱ አገዛዛቸውን
መቀጠል አይችሉም።

ከዚህ በመነሳት የመኢሶን ትችት የሚለው አንድ ቁምነገር አለ። በአሁኑ ወቅት በአ
ለም አቀፍ ደረጃ የግሎባላይዜሽንና የነጻ ገበያ አራማጆችም ወያኔ መሬትን የግል የሚያደ
ርግና የመሸጥና መለወጥ መብትን የሚያረጋግጥ ለውጥ እንዲደረግ ሃይለኛ ግፊት እያደረ
ጉ ናቸው። ጫናው ከቀጠለ ወያኔ ያለው ምርጫ ወይ የይዞታ ዋስትና አረጋግጦ በገበሬው

ላይ ያለውን የፖለቲካ ቁጥጥር ጨርሶ ማንሳት ወይ ደግሞ አሳዳሪዎቹ የሚያዙትን የግል
ሃብት አማራጭ መቀበል ይሆናል። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያመቸው ይህንን ሁለተ
ኛውን አማራጭ መያዝ ነው። በዚህ መልክ በነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ስም በህገ ወጥ ኩባንያዎ
ቹ አማካኝነት የከተማውን ኢኮኖሚ እንደተቆጣጠረ ሁሉ የገጠሩንም ኢኮኖሚ መዳፉ ው
ስጥ ሊያስገባ የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት ተቃዋሚ ድር
ጅቶች ዛሬ ባለው ሁኔታ በግርግር እንዲህ አይነቱ «መመለሻ የሌለው» ለውጥ በወያኔዎች
ለወያኔዎች እንዳይደረግና የገጠሩንም ኢኮኖሚ ለወያኔዎች አስረክበን ስዶ ማሳደድ ሁኔታ
ውስጥ እንዳንገባ በጥንቃቄ እንዲራመዱ፤ ለጊዜው ሁሉም እዛው በዛው ገበሬውን ከወያኔ
የፖለቲካ መዳፍ ነጻ አውጥቶ ሃገራችንን ለመጀመሪያ ጊዜ ለእውነተኛ ነጻ ምርጫ ለሚያ
መቻች፤ በኢኮኖሚው መስክ ምርት ለማሳደግ ለሚያበረታታና በአካባቢ እንክብካቤም በኩ
ል የእያንዳንዱን አራሽ ተሳትፎ ለሚያሳድገው የይዞታ ዋስትና እንዲታገል ጥሪ ተላልፉዋ
ል።

እነኢዴፓ በዚህ መድረክ ላይ አማራጭ ብለው ያቀረቡት መሬት የግል ሃብት የሚ
ለውን ለውጥ ነው። በዚህ አካሄድ የማንስማማው ከገበሬው ዘጠና በመቶ የሚጨነቅበትን
የይዞታ ዋስትና ጥያቄ ወደ ጎን ትተው ሰላሳ ሁለት በመቶ ብቻ የሚደግፈውን የግል ሃብት
ጥያቄ በማንሳት ገበሬውን ያልበላው ቦታ በማከካቸው ብቻ አይደለም። ነገ ዴሞክራሲና የ
ህግ የበላይነት ሰፍነው ዋናዎቹ ባለጉዳዮች የሆኑት የሃገራችን ገበሬዎች በጥሞና መክረው
ከፈለጉ ሊያመጡት የሚችሉትን ለውጥ ዛሬ በግርግር በወያኔዎች ለወያኔዎች እንዲደረግ
ጥሪ በማድረጋቸውም ብቻ አይደለም። የማንስማማበት አንዱ መሰረታዊ ምክንያት ስዶ ማ
ሳደድ እንዳይሆን ተብሎ የቀረበው ማስጠንቀቂያ በዚህ መድረክ ላይ በግልጽ ሲንጸባረቅ በ
መታዘባችን ነው።

በመጀመሪያው ከአቶ መለስ ጋርም በተዘጋጀው መድረክም ሆነ ባለፈው ሳምንት ከነ
አቶ በረከት ስምኦን ጋር በተካሄደው ክርክር የኢዴፓ ዋና ጸሃፊ አቶ ልደቱ አያሌው ሁለ
ት መሰረታዊ ጥያቄዎች አንስተዋል። በአንድ በኩል ወያኔ በከተማው የግል ኢኮኖሚ ዘር
ፍ የተከለው ቁጥጥር እንዲያከትም ህገ ወጥ ኩባንያዎቹ እንዲፈርሱ ጠይቀዋል። እንደሰ
ማነው ከሆነ አቶ በረከት ስምኦን ለዚህ ለአቶ ልደቱ ጥያቄ የሰጡት መልስ እናቱዋም አባ
ቱዋም «ክሰሱን» የምትል ቀጭን መልስ ነበረች። ይኸ የሚያስገርም ነገር የለውም። የሚ
ያስገርመው ነገር ወያኔዎች የከተማውን የግል ኢኮኖሚ መስክ ከመዳፋቸው ያስገቡት በፕ
ራይቬታይዜሽንና በነጻ ገበያ ስም እንደሆነ እየታወቀ የኢዴፓው መሪ ዛሬ በወያኔ ሙሉ ቁ
ጥጥር ስር ባለች አገራችን ነጻ ገበያና ፕራይቬታይዜሽን ወደ ገጠሩም እንዲዛመት ያደረጉ
ት ጥሪ ነው።

ባለፈው ሳምንት ያስደመጥነው የመኢሶን ትችት መሬት የግል ሃብት ብለን የገጠሩን
ም ኢኮኖሚ እንደከተማው ለወያኔዎች እንዳናስረክብና ስዶ ማሳደድ እንዳይሆንብን የሚል
ማስጠንቀቂያ አዘል ትችት ነበር። በዚህ በኢንተር አፍሪካ መድረክ ላይ የተሳተፉት ተቃዋ
ሚ ድርጅቶች ያንጸባረቁትን አቋዋም ስናይ ሌላ መልእክት የለንም። ባጭሩ እኛም እውነ
ትም ስዶ ማሳደድ እንዳይሆንብን እንጠንቀቅ እንላለን።